www.fsc.gov.et

የሰበር መ/ቁ/158613

ሐምሌ 18 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች ፡ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ማስተዋል ሰፈረ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ አማራ ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ተጠሪ ለችሎት ስራ እንቅፋት ሆናለች በማለት ጥፋተኛ ናት በሚል የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይህም ከማህደሯ ጋር እንዲያያዝ ትእዛዝ በመስጠቱ እና አመልካች ይህንን ትእዛዝ ለማስለወጥ አቤቱታ በማቅረቧ የስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ አግባብነት ከወንጀል ህግ አንቀጽ 449 አንጻር ለመመርመር እንዲቻል ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበ ነዉ፡፡

እኛም የቀረበዉን አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዘት እና አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ፍርድ ቤቱ ለትእዛዙ መሰረት ያደረገዉ መነሻ ምክንያት አመልካች የፍርድ ቤቱ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆና ለዳኞች የሚሰጥ የሞባይል ካርድ ለዳኞች ቢሮ ድረስ ለማቅረብ ፈቃደኛ አልሆነችም በሚል ምክንያት ጉዳዩን ችሎት ቀርባ እንድታስረዳ ስትጠራም ችሎት ለመቅረብ እምብተኛ ከመሆኗም በተጨማሪ በፖሊስ ተጠርታ ስትቀርብም ተገቢዉን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኗ ለችሎት ስራ እንቅፋት ሆናለች በሚል ምክንያት

www.fsc.gov.et

የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣትና ከማህደሯ እንዲያያዝ ትእዛዝ ስለመስጠቱ ገልጧል፡፡ችሎቱ ይህንን የቅጣት ዉሳኔ ሲሰጥ የህግ መሰረቱ ግልጽ ባለመሆኑ አከራካሪ ሆኖ ቀርቧል፡፡ለዚህም ነዉ በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 449 አንጻር አግባብነቱን መመርመር ያስፈለገዉ፡፡

በመሰረቱ የዳኝነት ስራ አካሄድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ዓይነትና ቅጣታቸዉ የሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 443 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ እንደተመለከተዉ እንደጉዳዩ ባሕርይና ጥፋት ዓይነት ቅጣት የሚጣልበት ሲሆን በተለይ ችሎት መድፈርን አስመልክቶ ችሎቱ በያዘዉ መዝገብ ላይ ወዲያዉኑ ቅጣት ሊወስን የሚችልበት አግባብ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 449 እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/480 እና 481 በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡የእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትም ሲታይ የዳኝነት ስራ በማከናወን ያለዉን ዳኛ በማናቸዉም መንገድ ማወክ፣መስደብ ፣ማፌዝ፣ መዛትና በመሰል ሁኔታ እንቅፋት መፍጠር እንዲሁም የዳኝነት ስራ አካሄድ ስነስርዓት አለማክበር፣ለችሎቱ ክብርና ለዳኝነት ስራ መልካም አመራር ተቃራኒ የሆነ ጠባይ የሚያሳይ ማንኛዉም ሰዉ ፣ የችሎት ተግባርና ስራ የሚያደናቅፋና ተገቢዉን ክብር ለማይሰጡ ለማይታዘዙና ተገቢዉን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆን የችሎቱን ስራ የሚያደናቅፍን ማንኛዉም ሰዉ በዚያዉ መዝገብ ወዲያዉኑ ተገቢ ቅጣት መጣል የሚያስችል ነዉ፡፡የነዚህ ድንጋጌዎች ዋነኛ ዓላማ የችሎቱን ስራ አካሄድ በማስከበር ያለእንቅፋት የዳኝነት ስራዉን ማሳለጥ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በዚህ መዝገብ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የሞባይል ካርድ ለችሎቱ ዳኞች የማቅረብ አስተዳደራዊ ግዴታ ወይም የስራ ሃላፊነት አልተወጣችም በሚል ምክንያት ወደ ችሎቱ እንድትጠራ መደረጉ የተገለጸ ሲሆን ከጅምሩ አስተዳደራዊ የስራ ሃላፊነት አለመወጣት አለ ከተባለ በአስተዳደራዊ ስነ ስርዓት ጉዳዩ ተጣርቶ ተገቢዉ እንዲወሰን ማድረግ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ከዚህ አልፎ ግን ችሎቱ ምክንያቱን ለመገንዘብ ፈልጎ ወደ ችሎት እንድትቀርብና ተገቢዉን ምላሽ እንድትሰጥ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ አመልካች ችሎት ቀርባ የችሎቱን ትእዛዝ አልቀበልም ማለቷ እንዲሁም ለችሎቱ ተገቢዉን ክብር አለመስጠቷ ከተረጋገጠ እና ችሎቱ ይህ ተግባሯ ጥፋት ነዉ ብሎ ካመነበት ቅጣት ሊወስን የሚችለዉ ለድርጊቱ ማቋቋሚያ ድንጋጌ በመለየት በወ/ህጉ

አንቀጽ 443 ወይም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 480 ወይም 481 በተደነገገዉ አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ከዚህ ዉጪ በህግ በግልጽ ባልተደነገገ አግባብ የሚጣል ቅጣት የህግ መሰረት የለዉም ፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጥና ይህም ከማህደሯ ጋር እንዲያያዝ በማለት የሰጠዉ የቅጣት ዉሳኔ የህግ መሰረት የሌለዉ ስለሆነ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ነገርግን አመልካች የፈጸመችዉ ድርጊት በአስተዳደራዊ መንገድ ተጣርቶ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበት ነዉ ወይስ የችሎቱን ስራ መድፈር ነዉ? በሚለዉ ላይ በመለየት ተገቢና አስተማሪ ዉሳኔ መስጠትን ይህ ዉሳኔ ቀሪ አያደርገዉም ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ትእዛዝ ሰጥተናል፡፡

## <u>ትእዛዝ፡፡</u>

1ኛ/የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ/03-75294 በ11/08/2010 ዓ.ም አመልካች ላይ የሰጠዉ የቅጣት ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

2ኛ/ አመልካች የፈጸመችዉ ድርጊት በአስተዳደራዊ ስነስርዓት ወይም በችሎት መድፈር የሚሸፈን ነዉ የሚለዉን በመለየት ተገቢዉን የመወሰን ጉዳይ ይህ ዉሳኔ ቀሪ አያደርገዉም ብለናል፡፡

3ኛ/ይኸዉ እንዲታወቅ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

ሰ/ጌ